# <u>የተሰጠን፡ መንፈስ - ራስን፡ መግዛት</u>

ባለፉት፡ ሁለት፡ ሳምንታት፡ የተሰጠን፡ መንፈስ፡ የኃይል፡ መንፈስና፡ የፍቅር፡ መንፈስ፡ እንደሆነ፡ ተመልክተናል። ዛሬ፡ ደግሞ፡ ሶስተኛውን፡ ሃሳብ፡ እንመለከታለን። እግዚአብሔር፡ የሰጠን፡ መንፈስ፡ ራስን፡ የመግዛት፡ መንፈስ፡ ነው። እራስን፡ መግዛት፡ እጅግ፡ የከበረ፡ ነገር፡ ነው። መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ስለዚህ፡ ጉዳይ፡ ሲናገር፡ እራሱን፡ የሚገዛ፡ ሰው፡ ከተማን፡ በኃይል፡ ከሚወስድ፡ ሰው፡ ይበልጣል ይላል (ምሳሌ 16፡ 32)። ከተማን፡ መያዝ፡ ከባድ፡ ነገር፡ ነው። ነገር፡ ግን፡ እራስን፡ መግዛት፡ ከዚያ፡ ይበልጣል።

እራስን፡ መግዛት፡ ማለት፡ ፍቃድን፡ መግዛት፡ ማለት፡ ነው። ፍቃድ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰዎች፡ የሰጠው፡ ነጻነት፡ ነው። የሰውን፡ ፈቃድ፡ ማንም፡ አስገድዶ፡ ሊጠመዝዘው፡ አይችልም። ሰው፡ እራሱ፡ ወደሚፈልገው፡ ያዘነብለዋል። በፍቃዳችን፡ እግዚአብሔርን፡ ልናመልክ፡ እንችላለን፤ ወይንም፡ ለክፉ፡ መጠቀሚያ፡ ልናውለው፡ እንችላለን። እራስን፡ መግዛት፡ ማለት፡ በፈቃዳችን፡ /ሳንገደድ/ መልካም፡ የሆነውን፡ ለማድረግ፡ መምረጥ፡ ማለት፡ ነው። ይህ፡ ደግሞ፡ በለት፡ ተለት፡ ሕይውታችን፡ በሚገጥሙን፡ የተለያዩ፡ ፈተናዎች፡ ሊገለጥ፡ ይችላል። ሄዋንን፡ እንደ፡ ገጠማት፡ አይነት፡ አስጎምጂ፡ የሃጢያት፡ ግብዣ፡ ሊቀርብልን፡ ይችላል። ወይንም፡ ጌታ፡ ኢየሱስን፡ እንደ፡ አጋጠመው፡ በተለያየ፡ መልኩ፡ የሚገለጥ፡ የዲያቢሎስ፡ ሽንገላ፡ በፊታችን፡ ሊሆን፡ ይችላል። እንዲህ፡ አይነቱን፡ መሰናክል፡ ለማለፍ፡ እራስን፡ በመግዛት፡ ኃይል፡ እንቢ፡ ማለት፡ መቻልን፡ ይጠይቃል። አንዳንድ፡ ጊዜ፡ ደግሞ፡ እራስን፡ መግዛት፡ የሚፈተነው፡ በተንኳሽ (provocative) ሁኔታ፡ ውስጥ፡ ስንገባ፡ ነው። በተለያየ፡ መልኩ፡ ስንተነኮስ፡ አንዱ፡ የሚመጣልን፡ ነገር፡ አጸፋውን፡ መመለስ፡ ሊሆን፡ ይችላል። እራሱን፡ የሚገዛ፡ ሰው፡ ግን፡ እንደበቱንም፡ ስለሚገዛ፡ የማይስማማበትን፡ ሃሳብ፡ ቢገልጥም፡ እንኳ፡ ንግግሩ፡ በጨው፡ እንደ፡ ተቀመመ፡ ለሚሰሙት፡ ጸጋን፡ ይሰጣል።

እራስን፡ መግዛት፡ የምናስበውን፡ ነገር፡ የመምረጥም፡ ጉዳይ፡ ነው። ከዚህ፡ በፊት፡ እንዳየነው፡ ሰው፡ እንደሚያስበው፡ እንደዚያው፡ ነው። ስለዚህ፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ መልካም፡ የሆነውን፡ ነገር፡ እንድናስብ፡ ያስተምረናል (ፊሊ 4፡ 8)። የምናስበው፡ ነገር፡ ደግም፡ ከምናየው፡ ነገር፡ ጋር፡ የተቆራኘ፡ ነው። ማየት፡ ወደ፡ ማሰብ፡ ያመጣል። ማሰብ፡ ደግም፡ ወደ፡ ድርጊት፡ ያመራል። እራስን፡ መግዛት፡ እንግዲህ፡ የምናየውን፡ ነገር፡ የመወሰንም፡ ጉዳይ፡ ነው።

ወገኖቼ፡ የተሰጠን፡ መንፈስ፡ እራስን፡ የመግዛት፡ መንፈስ፡ ነው። በውስጣችን፡ ያለው፡ መንፈስ፡ ልክ፡ ኮንፓስ፡ መርከብን፡ ወደ፡ ምትፈልገው፡ አቅጣጫ፡ እንደሚመራት፡ እንዲሁ፡ መንፈስ፡ ቅድስ፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ፅድቅ፣ ቅድስናና፡ ሰላም፡ ይመራናል። ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጋር፡ ያለን፡ ሕብረት፡ በጠነከረ፡ ቁጥር፡ እርሱ፡ ወደ፡ ሚፈልገው፡ አቅጣጫ፡ ይመራናል። በሕዝቅኤል፡ ላይ፡ የተመለከተው፡ ከመቅደሱ፡ ወጥቶ፡ የሚፈሰው፡ ውሃ፡ መጀመሪያ፡ ከነብዩ፡ ቁርጭምጭሚት፣ ቀጥሎም፡ ጉልበቱ፡ ጋር፡ ከዚያም፡ ወገቡ፡ ጋር፡ እንደ፡ ደረሰና፡ በመጨረሺያም፡ ሊሻገሩት፡ የማይቻል፡ ወንዝ፡ እንደ፡ ሆነ፡ የመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ሙላትም፡ እንዲሁ፡ በሕይወታችን፡ እየጨመረ፡ ይሄድና፡ በመጨረሻ፡ ሁለንተናችንን፡ ይቆጣጠረናል። ያን፡ ጊዜ፡ መንፈስ፡ በስጋ፡ ላይ፡ ፈጽሞ፡ ስለሚያይል፡ ምርጫችንን፣ ንግግራችንንና፡ አካሄዳችንን፡ ሁሉ፡ እርሱ፡ (ጌታ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ) ይገራዋል። ስለዚህ፡ በተከታታይ፡ እንዳየነው፡ በህይወታችንና፡ በአገልግሎታችን፡ ሁሉ፡ የእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ እንዲገለጥ፤ በፍቅር፡ እንድናድግና፡ እራስን፡ የመግዛትን፡ ፍሬ፡ እንድናፈራ፡ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ጋር፡ ያለንን፡ ሕብረት፡ ማጠናከር፡ ይገባናል።